# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)


## <u>እንኳን አደረሳችሁ!</u>

እነሆ ፲፱፻፺፰ ዓ/ም እንዳጀማመሩ የፈተኛ፥ የመከራ፥ የፍዳ፥ የእስርና እንግልት፥ የመብት መረገጥና የከፍተኛ አደጋ ሆኖ መጠናቀቁ ነው። ይኽ የምንሰናበተው ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት ፺፯ ዓ/ም ያስመዘገባቸውን ድሎች የተነጠቀበት፥ የኢሕአዴግ የሽብር አምባ-ገነናዊ አገዛዝ በውድ አገራችን በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ የሽብር ሥርዓቱን ያንሰራፋበት፥ ፍጹም አፈና፥ አፈሳ፥ ጭፍጨፋ፥ ግዞት፥ ስደት፥ እረሃብ፥ የኅርፍ መጥለቅለቅ፥ ወዘተ ... የታዩበትና የቀጠሉበት የስቃይ ዓመት ነበር።
እንዳይመለስ የምንሰናበተው አዲስ ዓመት አገራችንን ለማያባራ ድህነትና ለችግር የዳረገውን የአምባ-ገነን ሥርዓት አብሮ ቢሰናበተው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምኞት ቢሆንም እነሆ አብሮን ሊሽጋገር ነው። ችግሩና መከራው የመበራከቱን ያህል በአንፃሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተነጠቁ መብቶቹንና የግንቦት ድሎቹን  ለማስከበርና ለማስጠበቅ፥ በትግሉ ከላዩ ላይ አውልቆ ወደጣላቸውና ወደሻራቸው የመከፋፈልና የአምባ-ገነኖች ሥርዓት አዙሪት ላለመመለስ ከአሸባሪ አምባ-ገነኖች ጋር የተያያዘውን ትግል በምሬትና በቁርጠኝነት የቀጠለበት የትንንቅ ዓመት ነበር። ተፈቅሮና ተወድዶ መከበርን ሳይሆን ተፈርቶ መኖርን የመረጡት የኢሕአዴግ አሸባሪ አምባ-ገነኖች ያለ የሌለ የጥፋት ኃይላቸውን በሕዝባችን ላይ አሰማርተው ወገን ይሰራዋል ተብሎ የማይጠበቅ ግፍ መፈጸማቸው የባሰ ከሕዝብ እንዲርቁ፥ የበለጠ እርቃናቸውን እንዲቀሩ፥ ከቀን ወደ ቀን የበለጠ በስጋት ውስጥ እንዲኖሩ፥ እንደ ባዕድ እንዲታዩ አደረጋቸው እንጅ የተሻለ ሁኔታን እንኳን ለአገር ለራሳቸውም አልፈጠሩም። ይኽ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አምባ-ገነኖች የአመፅና የኃይል ይዞታቸው የሚያሳየው ጥንካሬአቸውን ሳይሆን ግብዝነታቸውንና ከፍተኛ ደካማነታቸውን ብቻ ነው።

አዲሱን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም ስንቀበል በ፲፱፻፺፰ ዓ/ም ለመልካም ሥርዓት እውን መሆንና ለመብት መከበር መቆማቸው ብቻ እንደወንጀል ተቆጥሮ በግፍ የተገደሉና የወደቁ ሰማዕታትን፥ በየእስር ቤቱና በየማጎሪያ ጣቢያው ይኽ ነው ተብሎ ሊገለጽ የማይችል ግፍ የደረሰባቸውና እየተሰቃዩ የሚገኙ የድርጅት መሪዎችን፥ ጋዜጠኞችን፥ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ንጹኃን ዜጎችን፥ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ደግፋችኋል ተብለው የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን፥ ከሥራቸው የተፈናቀሉትን፥ ማሳቸውን የተቀሙትን፥ የንግድ ፈቃዳቸውን የተነጠቁትን በርካታ ዜጎችን፥ ልጆቻቸው፥ ጓደኞቻቸው፥ ወዘተ... የት እንደወደቁ መዳረሻቸውን ባለማወቅ እ-ህ-ህ- የሚሉ ወላጆችና ቤተሰቦችን፥ ከቤተሰባቸውና ከሚወዷት አገራቸው ተለይተው ለአዲስ ዙር  ስደት የተዳረጉ ዜጎችን፥ በሌባኖስም ሆነ በሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ወድቀው የቀሩ ወገኖችን፥ ለጎርፍና ለረሃብ ሰለባ የሆኑ ወገኖችን፥ ወዘተ.. ሁሉ በኅሊናችን ይዘንና ከፍተኛ ተሃስቦአችንን፥ አክብሮታችንንና አድናቆታችንን እየገለጽን ነው።

ለፍትኅና ለመብት የሚደረግ ሕዝባዊ ትግል እንደመልካም ጠጅ ጊዜው ሲራዘም ይከርራል፥ ይጠነክራል እንጅ አይኮመጥጥም፥ አጉል አይሆንም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አምባ-ገነኖችና ተሳፋ ኮስማና ግብዞች እንደሚመኙት ሊከስም ከቶውንም አይችልም። መስዋዕትነቱ ቢበዛም የበለጠ ሥር እየሰደደ፥ እየጎመራና ለአይቀሬው ትግል እራሱን እያመቻቸ ይቀጥላል። በዚህ አስቸጋሪና ፈታኝ ጊዜ በኢሕአዴግ አሸባሪ አምባ-ገነኖች ፀረ-ሕዝብ እርምጃ ሰለባ የሆነው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የበለጠ እየተወሳሰበ መሄዱ ቢያሳዝንም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳየው ቁርጠኝነት፥ ሽብርን መቋቋም ብቻ ሳይሆን


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

ድል አድርጎ አገራችን አንድነቷ ተጠብቆ ፍትኀ፥ እኩልነትና የሕግ የበላይነት የሰፈኑባት አገር እንደምትሆን ያለንን እምነት የበለጠ አጠናክሮታል። የበለጠም ቆርጠን እንድንሰለፍ የትግል ቃል ኪዳናችንን እንድናድስ አድርጓል።

ትግሉ ቀላል መስዋዕትነትን የሚጠይቅ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ሆኖም ታጋይ የዴሞክራሲና የአንድነት የለውጥ ኃይሎች ካለፈው ዓመት ትምህርት ቀስመው፥ የተሻለ ተደራጅተውና ትግላቸውን አስተባብረው ኢሕአዴግን ወደ ድርድር እንዲመጣ ማስገደድ፥ ይኸን በጎ አሳብ ካልተቀበለ አገራችንና ሕዝባችን አንድነት ላይ ሳይሆን አገዛዙ ላይ ያነጣጠረ አማራጭ ይዘው በመንቀሳቀስ የሕዝቡን ትግል ለድል ሊያበቁት ይገባል።
በአገራችን በኢትዮጵያ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚታገሉ የዴሞክራሲ ኃይሎች በመኻላቸው ካለው ጊዜአዊ የፖለቲካ ልዩነት ይልቅ የአገሪቱንና የሕዝቧን ዘለቄታዊ ጥቅም በማስቀደም ትግላቸውን አስተባብረው የመቀጠላቸው አስፈላጊነት ከመቸውም ጊዜ የበለጠ አሁን ወቅታዊና አንገብጋቢ ሆኗል። የሕዝባችንን የሰቆቃ ጊዜ ለማሳጠርና አገራችንን ከተደገሰላት የከፋ ትርምስ ለማዳን የጋራ ትግሉ "በጠላቴ ጠላት" አጉል ዘይቤ ሳይሆን በነጠረና ግልጽ በሆነ አገራዊና ሕዝባዊ መርኆ ላይ የተመሠረተ ትብብርና የትግል አንድነት ሊኖር ይገባል። መተክላዊ ትብብር ለአስተማማኝ ድል አስፈላጊ ነው። የዛሬውን ብቻ ሳይሆን የነገውንና የተነገ-ወዲያውን ያዬ፥ ለጊዜአዊ የፖለቲካ ዋጋነት ሳይሆን ዘለቄታውን የጋራ ጥቅም ያገናዘበ የጋራ ትግል ማድረጉ ለፖለቲካ ድርጅቶች የአዲሱ ዓመት ውሳኔ እንደሚሆን ተስፋችን ነው።

የኢትዮጵያ የፖሊስ፥ የፀጥታና የአገር መከላከያ ሠራዊት አባላት በጣም አደገኛ ከሆነ ጠባብ ቡድናዊና ጎሣዊ አመለካከት፥ በኖ ከሚጠፉ ጊዚያዊ ጥቅማ ጥቅምና ፍላጎት በላይ የአገራቸውና የሕዝባቸው አንድነትና ሁላችንንም በእኩልነት፥ በፍትኅና በሕግ-የበላይነት ለሚያስተዳድር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን ይበልጥ ክብደትና ቅድሚያ በመስጠት የአምባ-ገነኖች ሥልጣንና ጥቅም አስከባሪ ሆኖ በታሪክም በሕግም ከመጠየቅ እራሳቸውን መቆጠብና ሰልፋቸውን በኢትዮጵያዊነት ስሜት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዲያደርጉ አደራችን የጠበቀ፥ ጥሪያችንም ወገናዊ ነው።

የኢሕአዴግ አገዛዝ የሕዝቡን ድምፅ አፍኖና ድሉን ቀምቶ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ባወጀው የሽብር ጦርነት ምክንያት መቀበል የሌለባችሁን ሁኔታ እንድትቀበሉ የተገደዳችሁና ውስጣችሁ እየበገነ የምትገኙ፥ የሕዝቡን አደራ በበሉ ክፍሎች ምክንያት ስሜታችሁ የተጎዳና መንፈሳችሁ የቆሰለ፥ በተቃዋሚው ጎራ መኻልና ውስጥ በሚታየው መጠነኛ እክል ቅሬታና ሃዘኔታ የተሰማችሁ፥ ለዴሞክራሲና ለሰብዓዊ መብት ቆመናል የሚሉ የውጭ ኃይሎች ቃላቸውን በአለመጠበቃቸውና ለጊዜው ከአምባ-ገነኖችና ከአፋኞች ጋር በመቆማቸው ግር የተሰኛችሁና ያዘናችሁ፥ ወዘተ... ወገኖቻችን ስሜታችሁ ስሜታችን ቢሆንም አፈናው ባስከተለው ጫና ምክንያት ለአንድነት፥ ለመብት መከበር፥ ለእኩልነትና ለፍትኀ የሚደረገው ትግል አገዛዙ እንደሚመኘው አለመክሰሙን እንድታውቁ እንፈልጋለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለው የለውጥ ፍላጎት ፈጽሞ ሊከስም አይችልም። ታጋይ ኃይሎችም ይኸ እንዲሆን አይፈቅዱም። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የቆመው ለተራ የሥልጣን ዝውውር ሳይሆን ለሥርዓት ለውጥ ስለሆነ፥ የሥልጣኑ ምንጭና ባለቤት ከሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ትግሉን ይቀጥላል። የሕዝቡ ትግል ለአስተማማኝ ድል እንደሚበቃ አንዳችም ብዥታ የለንም። አገዛዙ ያየው የላዩን ነበልባል እንጅ የውስጡን ረመጥ አይደለም። ሕዝባችን ፍላጎቱም ምኞቱም አሁንም ሰላም፥ የዴሞክራሲ ሥርዓት እውን መሆንና የመብቱ መከበር ጉዳይ ነው። ፍላጎቱና ምኞቱ እስከሚሳካም ባመቸው መንገድ ሁሉ ትግሉን ይቀጥላል፥ ቀጥሏልም። አንፃራዊ "ዝምታው" ሽንፈትን መቀበል እንዳልሆነ ምን ጊዜም ከሁኔታው ውጭ ከሚያስቡት የገኙው ክፍል አውራዎችና አቀንቃኞች በስተቀር ሁሉም ያውቀዋል።

በዓለም ዙሪያ የኅብረቱን ብሔራዊና ሕዝባዊ ዓላማ ለሚያራምዱ ታጋዮቻችንና ደጋፊዎቻችን ያለንን አክብሮት ስንገልጽ በአገር ውስጥ የሚደረገው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በዚህ አዲስ ዓመት የበለጠ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያለንን ተስፋና ዝግጁነት ስናሳውቅ በሙሉ እምነት ነው።

ኢዴኃኅ (ኅብረት) ባለፈው ዓመት ከታዩ አኩሪ አዎንታዊ ክስተቶች መኻል መቀጠልና መጎልበት የሚለው በውጭው ዓለም የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የትግል መንፈስና አገር-ወዳድነት ስሜት ነው። ይኽ ለገኸረው ክፍል የልብ ውጋትና የውስጥ እግር እሳት የሆነ እንቅስቃሴ በተሻለ ተደራጅቶ ለአገሩና ለሕዝቡ ያለውን አለኝታነት እንዲቀጥል የአክብሮት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

የአቶ መለስ ሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በግንቦት ፺፯ የተወለደው የመልካም ሥርዓት ግንባታ ተስፋ እንዲጨልም የቀጠለው ዘመቻ በአዲሱ ፲፱፻፺፱ ዓ/ም እንዳይቀጥል ብቻ ሳይሆን አገራችን በእርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ የሰከነ ሽግግር የሚደረግበትና ዴሞክራሲ ሥርዓት እውን የሚሆንበት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግሉ ዳግም ግንቦትን የሚያስገኝበት እንደሚሆን ተስፋችን የላቀ፥ ለዚህም ያለብንንና የሚጠበቅብንን ታሪካዊ ድርሻ ለመወጣት ያለንን ዝግጁነትና ቁርጠኝነት ለኅብረቱ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስንገልጽ ከአክብሮታዊ መልካም ምኞት ጋር ነው።

አዲሱ ዓመት አገራችን ኢትዮጵያ እርቅ የሚወርድበትና ዘለቄታዊ ሰላም የምታይበት፥ እስር ቤቶች የሚዘጉበት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወንድማማችነት/እህትማማችነትና አንድነት የሚጠናበት፥ የዜጎች መብት የሚከበርበት የድል ዓመት እንዲሆን ከልብ እንመኛለን።

አዲስ ዓመት ለአዲስ ተስፋ!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ጳጉሜ ፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም